ለርሱ ሁለት ሚስቶች ኑረውት ወደ አንዳቸው የተዘነበለ የትንሳኤ ቀን ጎኑ የተንሻፈፈ ሆኖ ይመጣል።

ከአቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው ነቢዩ (ሶለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና እንዲህ ብለዋል፦ "ለርሱ ሁለት ሚስቶች ኑረውት ወደ አንዳቸው የተዘነበለ የትንሳኤ ቀን ጎኑ የተንሻፈፈ ሆኖ ይመጣል።"
[رواه أبو داود والترمذي والنسائي وابن ماجه وأحمد] [ነው። ሶሒሕ[

ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ለርሱ ከአንድ በላይ ሚስቶች ኑረውት በመካከላቸው በሚያወጣው ወጪ፣ በቤት፣ በልብስና በማደር በሚስቶቹ መካከል የቻለውን ፍትህ ያላሰፈነ ሰው የትንሳኤ ቀን የሚቀጣው ግማሽ ሰውነቱ እንዲያንሻፍፍ በመደረግ እንደሆነ ተናገሩ። መንሻፈፉም ከሚስቶቹ ጋር በነበረው መስተጋብር እንደተዘነበለው ለሰራው በደል ቅጣት ነው።

http://www.sunnah.global/hadeeth/am/show/58125